አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሁለተኛ አመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2[tnd] year No. 3
Addis Ababa 9[th] of Novembetr, 2009

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፲፰/፪ሺህ፪**

**የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከልማቋቋሚያአዋጅ**
**አዋጅ--------------------ገፅ ፩**

**CONTENT**

PROCLAMATION FOR THE ESTABLISHMENT OF THE GULLELE BOTANIC GARDEN PROCLAMATION-------------------- Page 2

## አዋጅ ቁጥር ፳፯/፪ሺ፲፪

### የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከልማቋቋሚያ አዋጅ

ተፈጥሯዊመዝናኛ ቦታዎችን ጨምሮ ለተለያዩ ተግባራት የሚውል ዘመናዊ የእፅዋት እንክብካቤና የኢኮቱሪዝም አገልግሎቶችን የሚሰጥ ማዕከል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም በጉለሌና ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ በሚገኘው መሬት ላይ ልዩ መልከዓ ምድርን ከፍተና ዋጋ ያላቸው የስነ ሕይወታዊ ሐብቶችና ለአደጋ የተጋለጡ ዝርያዎችን በዘላቂነት ለመንከበከብና ለልማት ከላይ በተጠቀሰው ቦታ ዘመናዊ የዕዕዋት ማዕከል ለማቋቋም ያስፈለገ በመሆኑ፣

እንዲህ አይነት የእዕዋት ማዕከል መቋቋም በስነህይወት በተፈጥሮ ሀብቶች አያያዝ እና በሌሎች አካባቢዎች መስኮች ላይ ለሚካሄድ ትምህርታዊና ምርምር ስራዎች አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ፣

እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካትና የሕዝቡን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ዘላቂታዊ የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ጠቃሚ መሆኑን በማመን፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሸሻለ ቻርተር አዋጅ ቁጥር፫፻፳፭/፲፱፱፻፺፩ አንቀጽ ፲፬ (፩) (ሀ) መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## PROCLAMATION FOR THE ESTABLISHMENT OF THE GULLELE BOTANIC GARDEN

**WHEREAS,** its Essential to have a modern Botanic Garden that may be employed for a variety of services, including species conservation nature based eco-tourism facilities.

**WHEREAS,** the city Government of Addis Ababa is desirous of Establishing a Botanic garden, in an area located within the bounds of the unique landscaps, valuable biological resources and the indangered species inhabiting in the area,

**WHEREAS,** as the establishment of sucha garden will also lay down a conducive environment for educational and research work to be undertaken in the area of biodiversity and natural resources and other environment related fields.

**WHEREAS,** collaboration with higher learning and research institution is crucial to further these objective and bring about public awareness in the conservation and sustainable utilization of natural resources.

**NOW, THERFORE,** the city council of Addis Ababa in accotdance with Article 14/1/a of the Addis Ababa city Govermnt Revised charter proclamation No.36/2003 proclams as follows.

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፶፭ሸ፮፻፺፰
Addis Negari Gazeta P.O.Box 55698

ያንዱ ዋጋ..........7.80
Unit price..........

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፲፰/፪ሺ፲፪ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የዋሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር

፩. ማዕከል ማለት የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ነው፡፡
፪. የእጽዋት ማእከል ማለት በዚህ አዋጅ እና በሌሎች የፌደራል ወይም የከተማ ሕጎች መሰረት በተሰጠው ሃላፊነት መሰረት በጉለሌና በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተሞች ውስጥ በተሰጠው ፯፻፭ (ሰባት መቶ አምስት) ሄክታር መሬት ላይ ስራውን የሚያከናውን የጉለሌ የእጽዋት ማዕከል ነው፡፡
፫. ቦርድ ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የሚመሰረትና የእጽዋት ማእከሉን በበላይነት የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡
፬. ከተማ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡
፭. የከተማ አስተዳደር ማለትየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
፮. ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ማለት በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ ተግባራትን የሚያከናውን የማእከሉ ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ነው፡፡
፯. ዩኒቨርሲቲ ማለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡
፰. ምክር ቤት ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው፡፡
፱. ካቢኔ ማለት በተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፷፩/፲፱፺፭ አንቀጽ ፳፫ የተዘረዘሩ ተግባራትን የሚያከናውን የከተማው አስፈጻሚ አካል ነው፡፡
፲. የመማከር ካውንስል ማለት የጉለሌ የእጽዋት ማእከል መማከር ካውንስል ነው፡፡

**፫. መቋቋም**

፩. የጉለሌ የእጽዋት ማእከል ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
፪. ማእከሉ በቦርዱ በኩል ተጠሪነቱ ለከተማው አስተዳደር ከንቲባ ይሆናል፡፡

## PART ONE
## GENERAL

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as the Gullete Botanic Garden Establishment proclamation No18/2009

**2. Definition**

In this proclamation uncle the context provides otherwise.

1. Garden means the Gullete Botanic Garden
2. Botanic Garden means the 705/seben hindered five/ hectare area allocated within Gulete and kolfe keraniyo sub-cities designated fort he operation of the functions of the Garden over which it has full jurisdiction in accordance with the provisions of this proclamation and other Federal of city lows.
3. Board" means the government board of the Garden constituted in accordance with the provisions of this Proclamation.
4. City means the city of Addis Ababa
5. City Government means the city Government of Addis Ababa
6. Excutive Direction; means the excutive director of the Garden Who performs the functions which are listed in this proclamation.
7. University means the Addis Ababa University
8. Council means the Addis Ababa City Government Council.
9. Cabinet means the executive body of the city that perform function mentioned under Article 23 of the Addis Ababa city Government Revised charter proclamation No.361/2003
10. Advisory council means the advisory council of the Garden.

**3 ESTABLISHMENT**

1. The Gullete Botanic Garden is hereby Established by this proclamation as an independent legal entity
2. The Garden shall, through its board, be accountable to the Mayor of the city Government.

**፬. ዓላማዎች**

ማእከሉ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

፩. በማእከሉ በአካባቢው ወይም በኢትዮጵያና በሌሎች አካባቢዎች ለመጥፋት የተቃረቡ የዝርያዎች እንክብካቤ ተግባራትን ማከናወን፣

፪. በሥነ ሕይወት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በሌሎች አካባቢነክ መስኮች ላይ ምርምር ማካሄድ፣

፫. በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ የመዝናኛ የኢኮቱሪዝም አገልግሎት መስጠትና ማስፋፋት፣

፬. ከአካባቢ ጥበቃ ከተፈጥሮ ሀብትና ከሥነ ምህዳር አያያዝ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ግንዛቤ የመፍጠር ዓላማ ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ማመቻቸት መተግበር፣

፭. በአካባቢ ጥበቃ መስኮች የተሰማሩ ብሐየራዊና አለም አቀፋዊ የሲልቫ ማህብረሰብ ድርጅቶችን መደገፍና ማበረታታት፣

**፭. የማዕከሉ ተግባራትና ኃላፊነቶች**

የዕፅዋት ማእከሉ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

፩. የእጽዋት ማእከሉ የአጭር መካከለኛና የረዥም ጊዜ የልማት ፕሮጀክቶችንና የድርጊት መርሐ ግብሮችን መቅረፍና በቦርዱ ይሁንታ መተግበር፣

፪. በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብቶች ምህዳር እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ሥነ-ሕይወታዊ ሥነዐአካላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የምርምር ስራዎችን ማካሄድ

፫. ለእጽዋት ማእከሉ የተከለለው ቦታ የእጽዋት አይነትና የመሬት አጠቃቀም ዝርዝር ጥናት በጊዜው ማካሄድ እና መተግበር፣

፬. ለዘላቂ ምርቶችና አገልግሎቶች በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ በኢኮቱሪዝም ልማትና በታዳሽ የኃይል ምንጮች ምርምርና አቅርቦት ሰርቶ ማሳያዎችን ማከናወንና ማበረታታት.

**4. objective**

The garden shall have the following objective.

1. Undertake activities related to conservation of threatened species that exist in the Garden and its catchments area as well as elsewhere in Ethiopia
2. Conduct research on biodiverty, natural resource protection and other Environment related field
3. Provide and extend natural based recreation and eco-tourism services to the public.
4. Conduct and facilitate educational programs and projects that aim at creating public awareness on matters pertaining to environment protection and eco-systems management.
5. Encourage and support national and international civil society organizations working in the area of environment protection and related activities.

**5 Functions and Responsibilities of the Garden**

The Garden shall have the following functions and responsibilities.

1. Formulate short, medium and long-term development projects and action plan and implement the same upon approval by the Board.
2. Conduct search on Environment and natural resources, as well as related biological, biophysical and sociological issues.
3. Conduct periodic research on species and land use in the Garden area.
4. Promote activities that stimulate the development of new valve chain, products and services particularly in horticulture, tourism, encourage research and demonstration of renewable energy sources.

፭. በዕፅዋት ማእከሉ አካባቢ የሥነ ምህዳርጥናት ማመቻቸት ከብዙሃን ሕይወት እንክብካቤና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎችን ማከናወን

፮. የዘመናዊ የእጽዋት ማእከል ተግባራትን ማከናወን፣

፯. ለአካባቢ ጥበቃ እና ምርምር እንክብካቤ የሚደርጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማበረታታትና መደገፍ፣

፰ አግባብነት ያላቸው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ቴክኒኮች እና ውጤታማ የተፋሰስ አያያዝ ዘዴዎችን ማሰራጨት

፱. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትን ዓላማዎች ለማሳካት ከሚከተላቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም ከዩኒቨረሲቲ ጋር በቅርበት መስራት፣

፲. ለሰራተኞች እና ካላማዎቹጋር ተያያዥነት ባላቸው ስራዎች ውስጥ ለሚሳተፉ ግለሰቦች የስልጠናና የክህሎት ማሳደጊያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣

፲፩. ውሎችን መዋዋል፣ ንብረቶችን በባለቤትነት መያዥ እርዳታ እና ስጦታዎችን መቀበል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፣

፲፪. የማእከሉ የሰው ኃይል ንብረትና ገንዘብ ማስተዳደር

፲፫. በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ማከናወን፣

**፮ <u>ንብረት የመረከብ</u>**

፩. የማእከሉ አስተዳደር በእጽዋት ማእከሉ ክልል ውስጥ በግለሰቦች እና በድርጅቶች በሕጋዊነት የተያዙ ንብረቶችን ስለመረከብ መመሪያ ያዘጋጃል በቦርዱና በከተማው አስተዳደር ይሁንታ ሲያገኝ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

5. Undertake studies on the eco-system in the Garden area and engage in works related to bio-diversity conservation and environmental protection.
6. Perform modern botanic garden activities
7. Encourage and assist the activities of civil society organizations that cater to environmental protection and research.
8. Disseminate to the public appropriate soil and water conservation technique as well as effective watershidmanagment method.
9. Closely work with relevant higher learning institution,particularly with the University, for the attainment of the objective specified in this proclamation
10. Undertake training and skill upgrading programs to its personnel and those engaged in works related to its objective.
11. Conclude contract, own properties accept donations and legacies and sue and to be sued.
12. Manage its human ,asset and financial resources.
13. Perform such other takes necessary for the attainment of its objectives and the discharge of its duties and responsibilities as are set forth in this proclamation.

**6. POWER to Expropriate**

1 The Garden Administration may prepare guideline's on the modalities of expropriating properties lawfully held by individual and organizations, and implement upon by the Board and city Government.

፪. ይህንን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እና በቦርዱ ይፋዊ ጥያቄ የከተማው አስተዳደር ለማእከሉ በተመደቡ ቦታዎች ላይ የሚገኙ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ለማእከሉ እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት ለሚከናወኑ ይዞታን የመውሰድ ወይም የማስተላለፍ እርምጃዎች የተነሳ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች አግባብ ያላቸው የፌደራል እና የከተማዋ ሕጎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የማእከሉ አደረጃጀትና ስራ አመራር**

**፯ ድርጅታዊ መዋቅር**

ማእከሉ የሚከተለው ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል፡፡

፩. የመማከር ካውንስል

፪. ቦርድ

፫. ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር

፬. የምርምርና ልማት እንዲሁም ትምህርትና መዝናኛ ዘርፎች ሁለት ምክትል ዳይሬክተሮች

፭. አስፈላጊ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች

፮. ቦርዱ በየጊዜው እንደአስፈላጊነቱ የሚያቋማቸው ሌሎች ቋሚና ጊዜያዊ አማካሪ ኮሚቴዎች ወይም ኮሚሽኖች

**፰. የመማከር ካውንስል**

ማእከሉ የሚከተሉት ተግባራት ያለው የመማከር ካውንስል ይኖረዋል፡፡

፩ የማእከሉን እድገትና ልማት በሚያግዙ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ገንቢ ምክር ይሰጣል፡፡

፪. በማእከሉ ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርትና ሌሎች መረጃዎች ላይ በመመስረት አስተያየቶችን ያቀርባል፡፡

፫. ካውንስሉ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፬. የቦርዱ ሰብሳቢ የካውንስሉ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፭. የማእከሉ ስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የካውንስሉ ጸሀፊ ይሆናል፡፡

2. Whenever it is found necessary and upon a formal request by the Board, the city Government may cause the expropriation of immovable property located in the locality designed as the area of the Garden.

3. The relevant Federal and City laws shall govern the settlement of disputes that arises from expropriation measures taken in accordance with the provisions of this Article.

**PAR TWO**

**ORGANIZTION AND MANAGEMENT OF THE GARDEN**

7. **Organizational structure**

The garden shall have the following organizational structure

1. Advisory Council
2. The board
3. The Excutive Director
4. Two Deputy Director for Research and development and for Education and Recreation
5. Other essential work unit and staff
6. Such other permanent that may be established by the board from time to time.

**8 ADVISORY Council**

The Garden shall have an Advisory council that performs the following

1. Render constructive advice on any case that helps for the growth and development for the Garden
2. Submit assessment based on the annualreports and other information
3. The councilshall meet once in a year
4. The chairperson of the Board shall be the chairperson of the advisor council
5. The Excutive Director of the Garden shall be the secreat of the advisory council.

**፱. የማማከር ካውንስሉ አባልነት**

፩. የመማከር ካውንስል በአካባቢ ጉዳዮች በአጠቃላይና በዕጽዋት ማእከል ልማት በተለይ ልምድና ፍላጎት ያላቸው የመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሙያና ህዝባዊ ማህበራት የአለም አቀፍና ዲፕሎማቲክ ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦችን በአባልነት ያካትታል፡፡

፪. የአባላቱ ዝርዝር ለቦርዱ ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

**፲. የቦርዱ አባልነት**

፩. የቦርዱ አባላት በከተማው ከንቲባ የሚሰየሙ ሆነው የሚከተሉትን ይይዛል፡፡

ሀ/ የከተማው ከንቲባ-----------ሰብሳቢ

ለ/የዩኒቨረሲቲው ፕሬዘዳንት------ምክትል ሰብሳቢ

ሐ/ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ዴታ---- አባል

መ/ የአዲስ አበባ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ--- አባል

ሠ/ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲቱት ዋናዳሬክተር--------አባል

ረ/ የአዲስ አበባ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ-------አባል

ሰ/ የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ-------አባል

ሸ/ የዩኒቨርሲቲው የሳይንስ ፋኩሊቲ ዲን-------አባል

ቀ/ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ተወካይ-------አባል

በ/ ታዋቂ ግለሰቦች እና/ወይም ሳይንቲስቶች ፪----- አባል

ተ/ የማእከሉ ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር-----አባልና ጸሐፊ

**9. Membership of the Advisory Council**

1. The council shall constitute particularly governmental organization, NGOS, representative of professional and mass association, international organization and diplomatic missions and personalities that have experience and interest on environmental issues and botanic garden development in general.
2. List of the members shall be submitted to the Board for approval.

**10 Membership of the Board**

1. The Board members to be nominated by the city Mayor shall include the following
   a) The Mayor of the city---------------chairperson
   b) The president of the University --------------Deputy chairperson
   c) The Minister or the state minister of culture and tourism ---------member
   d) The head of the Addis Ababa culture and tourism bureau -----------member
   e) The chief director of the institute of biodiversity conservation ------------member
   f) The c chief manager of the Addis Ababa Environmental protection authority-----Member
   g) The chief executive office of the Gullet sub-city Administration --------member.
   h) The dean of the faculty of science of the University-------member.
   i) The Representative of the oromia region Government-------------member.
   j) Two prominent personalities and/or scientist-------------member.
   k) The Executive Director of the Garden---------member and secretary.

፪. የከተማው ከንቲባ እንደሁኔታው ለምክትል ከንቲባው ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፲፩. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

፩. አግባብነት ያላቸው የፌደራል እና የከተማዋ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው ማእከሉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ፡-

ሀ) የማእከሉ አጠቃላይ መመሪያ እና እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠር ፖሊሲዎቹን እና መርሀ ግብሮቹን በማመንጨት አፈጻጸማቸውን ለመወሰን እንዲሁም ከሶስተኛ ወገን ጋር ማእከሉ ሊመሰረት የሚችለው ግንኙነቶች መርምሮ ያጸድቃል፡፡

ለ) የማእከሉ ዓመታዊ የበጀት ጥያቄ እና ዋና ዋና መርሀ ግብሮች መርምሮ ያጸድቃሉ፡፡

ሐ) በስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተር የሚቀርብለትን የማእከሉን አመታዊ ስራ አፈጻጸም እና የበጀት አጠቃቀምን መርምሮ ያጸድቃል፡፡

መ) የማእከሉን የፖሊሲ ጉዳዮች ይመረምራል፡፡ ያጸድቃል፣ ከስልጣኑ በላይ የሆኑትን ለከተማው አስተደደር እንዲቀርቡ ደርጋል፡፡

ሠ) የማእከሉን ኦዲተር ይሾማል ዓመታዊ ሪፖርቱንም ያጸድቃል፡፡

ረ) የስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተርን ይመድባል፣ ያነሳል

ሰ) ተጠሪነታቸውን በቀጥታ ለስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሆኑትን የማእከሉን የስራ ሃላፊዎች በስራ አስፈጻሚው አቅራቢነት ይመድባል፣ ያነሳል፡፡

ሸ) የማእከሉን የውስጥ መመሪያዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ተመልክቶም ያጸድቃል፣አፈጻጸሙንም ይቆጣጠራል፡፡

ቀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት ከናውናል፡፡

2 the Mayor of the city may delegate the Deputy Mayor When necessary

**11.powers and functions of the Board**

1. subject to relative federal and city laws, the Board shall be the ultimate decision making body in matters pertaining to the Garden.

2. Without prejudice to the general provision of sub-Article 1 hereof, the Board shall

a) be responsible for the overall control of the activities of the Garden for the formulation of its policies programs, direction and implementation and supervision of the relationship that the garden may establish with third parties.

b) Investigate and approve the budget requires and major programs of the Garden.

C. deliberate upon and approve the annual progress of programs and financial reports of the Garden to be submitted to it by the Executive Director.

d) consider and Approve all policy matters of the Garden and sub

e) appoint Auditors of the Garden and Approve the annual reports of the auditors(s) of the Garden as well

f) appoint and remove the Excutive director

g) approve upon the recommendation of the excutive director the appointment and removal of officers of the Garden that are directly accountable to the excutive directors.

h) cause the preparetion of directives of the garden approve and follow up on the execution

i) perform such other function are are necessary for the attainment of the objective set forth in this

ፗ

ይቀርጻል፣ ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ በቦርዱ ሲፀድቅ ይፈጽማል፡፡

፲፪ የቦርዱ ስብሰባ

፩. ቦርዱ በዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪. የቦርዱ ልዩ ስብሰባ በሰብሳቢው ወይም ከአባላቱ 3/ኛው በጽሁፍ ሲጠይቁ ሊጠራ ይችላል፡፡

፫. የቦርዱ አባላት ሀምሳ አንድ ከመቶና ከዚያ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፬. የቦርዱ ውሳኔዎች ምልዓተ ጉባኤ በሚኖርበት ጊዜ በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይወስናል፡፡ እኩል-በእኩል ድምጽ በሚኖርበት ጊዜ የሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ድምጽ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡

፭. ቦርዱ የራሱ የስነ ስርዓት መርሆች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፫. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሥልጣን እና ተግባራት

፩. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የማዕከሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን ለፖሊሶች፣ ለቦርዱ ውሳኑዎች አፈፃፀም እና የማዕከሉን የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች በመምራት፣ በማቀድ፣ በማደራጀት እና በመቆጣጠር ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተገለፀው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ….. ሥር የተገለጹትን የማዕከሉ ተግባራት እና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

ለ) የማዕከሉን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ እቅዶች እና መርሀ ግብሮችን

12. Meetings of the Board

1. The Board shall meet at least four times in a year .
2. extraordinary meetings may be called by the chairperson or at the written request of one-third of its members.
3. fifty percent plus one and the above of the members of the Boardsshall constitute a quorum.
4. decisions of the board shall be made by a simple majority of members present at a meeting where there is a quorum. In the case of a tie, the chairperson shall having a casting vote.
5. The Board may issue its internal guidelines of procedure.

13. Power and fubnctions of the Executive Director

1. The executive director being the chief Excutive officer of the Garden and, in this capacity; he/she shall be responsible for the implementation of the policies and decisions of the Board as well as for directing, planning,, organizing and overseeing the day to day activities of the Garden.
2. Without prejudice to the general provision of sub-Article 1 hereof the Excutive Director shall perform the following functions:-

a) Carry out the functions and responsibilities of the Garden specified under Article 5 od this proclamation

b) Formulate, prepare or cause the preparation of short, medium and programs of the Garden and implement the same upon approval by the Board.

ሐ) ማዕከሉ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖሩት ጉዳዮች ሁሉ ማዕከሉን ይወክላል፣ ወይም ሌሎች እንዲወክሉት ያደርጋል፡፡

መ) የማዕከሉን በጀት ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ቦርዱ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፡፡

ሠ) የማዕከሉ የውስጥ መመሪያዎች እና የሥራ መርሀ ግብሮች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

ረ) በማዕከሉ የሚከናወኑ ሥራዎች ይቆጣጠራል፡፡

ሰ) የማዕከሉ የሰው ኃይል ንብረትና ሀብት ያስተዳድራል፡፡

ሸ) በዚህ አዋጅ ያለው ድንጋጌ እና የሀገሪቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የማዕከሉን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል ያሰናብታል፡፡

ቀ) በቦርዱ አመራር መሠረት የማዕከሉን የባንክ ሂሳቦች ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፡፡

በ) የማዕከሉን አግባብ ያላቸው የሂሳብ ደብተሮች ይይዛል ወይም እንዲያዙ ያደርጋል፡፡ ከማዕከሉ በፀደቀ በጀት እና የፋይናንስ መመሪያ መሠረት ወጪዎችን ይፈጽማል፡፡

ተ) በየጊዜው የስራ አፈፃፀም እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

ቸ) በማዕከሉ ለሚሰጡት የተለያዩ አገልግሎቶች የሚከፈሉ የአገልግሎት ክፍያዎች በቦርዱ ያስወስናል፤ ያስፈፅማል፡፡

ነ) የማዕከሉን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ፣ ግዥ እና ግንባታን በተመለከተ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውሎችን ይዋዋላል፤ የማዕከሉን ንብረት በመያዣነት በማስያዝ የብድር ውል ይዋዋላል፣ ከውጭና ከሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር ያሉ የምርመራና ሌሎች ውሎችን ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያስፈፅማል፡፡

ኘ) በማዕከሉ እና በዩኒቨርስቲው በጣምራ የሚከናወኑ የምርመራ ፕሮጀክቶችን እና ሳይንሳዊ ጆርናሎችን በመመስረት ያፀድቃል፡፡

አ) በቦርድ የሚሰጡት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

c. Reperesent the garden in all its dealings with third parties or cause such representation by other individuals.
d. Prepare or cause the preparation of the budget of the Garden, submit to the Board and implement the same up on approval by the Board.
e. Prepare or cause to be draw up the internal directives and work programs of the Garden.
f. Monitor works being undertaken in the garden area.
g. Adminster the hum,an resource, property and other resource of the Garden
h. Subject to the provision of this proclamation and having due regard to the relevanr laws of the land, employ, administer and dismiss employees of the garden.
i. Open and operate the bank accounts of the Garden in accourdance with the directives of the Board.
j. Maintain or cause to be maintained proper books of accounts of the Garden and effect expanses in line with the approved budget and financial manual of the Garden..
k. Submit periodic operations and financial reports to the Board.
l. Cause to be fixed by the Board fees payable on the various services offered by the garden to the general public; implement the same.
m. Conclude contracts with third parties in relation to the sale, purchase and construction of immovable property, to the borrowing of funds by offering the property of the Garden as Collateral; present to the Board and implement up on approval regarding research and other works with foreign institutions.
n. Establish and approve research projects and the establishment of scientific journals to be jointly undertaken by the Garden and the University.
o. Perform such other functions as may be assigned to it by the Board.

፫. የማዕከሉን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆኑ ድረስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የተወሰኑ ኃላፊነቱን ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለእርሱ ለሆኑ የማዕከሉ የስራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬. የሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል፡፡

**፲፬. የምክትል ዳይሬክተሮች ሥልጣን እና ተግባራት**

፩. የምርመራና ልማት ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶችን ያከናውናል፡፡

ሀ) የምርምርና ልማት ሥራዎችን ያቅዳል፣ ይፈፅማል፡፡

ለ) ሌሎች በስራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ሐ) እንደሁኔታው ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬከክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎ ይሰራል፡፡

፪. የትምህርትና መዝናኛ ምክትል ዳይሬክተር ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ) የማዕከሉ የትምህርት፣ የመዝናኛ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ያቅዳል ይተገብራል፡፡

ለ) እንደሁኔታው ሥራ አስፈፃሚ ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎ ይሰራል፡፡

ሐ) ሌሎች በስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሩ የሚሰጡት ተግባራት ያከናውናውናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የፋይናንስ አቅርቦት

**፲፭. የገንዘብ ምንጮች**

፩. የማዕከሉ የገንዘብ ምንጮች የሚያካትቱት በከተማው አስተዳደር በሚመደብ ጥልቅ የበጀት፣ በዩንቨርስቲው የሚገኝ ጥልቅ የበጀት ድጋፍ፣ ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎት ሊሰበሰቡ የሚችሉ የአገልግሎቶች ክፍያዎች፣ የማዕከሉን የምርምር ሥራዎች እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ስፖንሰር በማድረግ ከድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚገኝ ገንዘብ፣ እርዳታዎች እና ከካፒታል የሚገኝ ገንዘብ ቦርዱ በየጊዜው ወስኖ ከሚዘጋጂት ዝግጅቶች እና ሌሎች የገቢ ምንጮች ይሆናል፡፡

3. To the extent necessary for the efficient discharge of the duties and responsibilityes of the Garden, the Excutive Directors may delegate some of his/her powers under this Article to officials of the Garden who are directly accountable to him/her
4. The executive director shall be accountable to the Board.

**14. Powers and functions of the Deputy Directors**

1. The debuty director for research and development will be accountable to the executive director and will perform the following
   a) Plan and implements the Gardens research and estate development activities.
   b) Carry out other activities given by the executive director
   c) Represents the executive director as and when necessary
2. Ther deputy director for education and recearation will be accountable to the executive drector and will perform the following.
   A) Plan and implements of educational and recreational program.
   B) Carry out other activities given by the executive director
   C) Represent the executive Director as and when necessary.

## PART THREE

## PROVISIONS ON FINANCE

**15. Financial sources**

1. The financial sources of the graden comprise of inter alias, block grants to be allocated by the city government, funds to be made available by the university, fees the graden may collect for

the services it renders to the public, funds to be made available by organizations and individuals to sponsor its research and other project, donations and legacies, capital levies organization of events and such other sources as e Board may, from time to time deteremine



ለዚሁ አላማ በከተማው ቻርተር በተደነገገው ልዩ ተልዕኮው መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማዕከሉን ሁሉን አቀፍ ተግባራት እና እንቅስቃሴዎች የመደገፍና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፡፡



፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት ማዕከሉ ከማንኛውም ምንጭ የሚያገኘውን ገንዘብ ሁሉ በማዕከሉ ስም የተከፈተ የባንክ ሂሳብ የሚጠራቀም ሲሆን ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለማዕከሉ ሥራ ውጪ ይሆናል፡፡

**፲፮. የፋይናንስ አስተዳደር**

፩. የማዕከሉ ንብረት እና ፋይናንስ በሀገሪቱና በከተማው አስተዳደር የፋይናንስ አስተዳደር ህጎች መሠረት ይተዳደራል፡፡

፪. ማዕከሉ የተሟላ እና ትክክለኛ የሂሳብ ማግብት ይይዛል፡፡

፫. የማዕከሉ የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው አመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል፡፡

፬. ማዕከሉ ሂሳቡን ቢያንስ በአመት አንዴ ይዘጋል፡፡

**፲፯ ኦዲት**

፩. የማዕከሉ ኦዲተሮች በቦርዱ የሚሾሙ ሲሆን የማዕከሉን ሂሳቦች፣ መዛግብቶች፣ ሰነዶች እና ወረቀቶች ባልተገደበ ሁኔታ ማግኘት ይችላሉ፡፡

፪. ኦዲተሮች የኦዲት ተግባራቸውን በሀገሪቷ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባላቸው የሂሳብ ማጣራት ህጎች መሠረት የሚያከናውኑ ሲሆን ሪፖርታቸውን በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፰. ከተማውን አስተዳደር እና ዩንቨርስቲውን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች**

፩. የከተማው ነዋሪዎችን ሁለንተናዊና ብልጽግና ለማራመድ ካለበት ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነትና

2. The funds made available to the garden as per the provisoion of sub-Article 1 hereof shall be deposited in a bank account or anccounts opened in the name of the graden and shall be expended for the activities of the Garden in accordance with guidelines to be issued by the board.

**16. Financial Adminstration**

1. The property and finance of the garden shall be administered in compliance with nationally accepted laws of financial management.
2. The garden shall maintain complete and accurate books of accounts on a regular basis.
3. The fisical year of the graden shall commence on July 8 of the previous Ethiopian year and shall come to an end on June 7 of the following year.
4. The Graden shall close its accounts at least once a year.

**17. Audit**

1. The Auditor(s) of the garden shall be appointed by the board and shall have unrestricted access to the accounts, books, documents and papers of the Graden.
2. The Auditor shall cnduct their audit functions in compliance with nationally and internationally accepted laws of auditing and shall report their findings to the Board at least once a year

## PART FOUR

## MISCELANEOUS PROVISIONS

**18. Special provisions on the city Government the Universty**

1. In view of the constitutional and legal responsibility it has residents of the city and its special mission to this effct as refelected in the city charter the city Government shall be sponsible to overse the overall functions and e actives of the Garden

፲፪

## የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ



፪. በመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራ ካለው የረጅም ጊዜ ልምድ እንዲሁም በሰው ኃይል እና በቁሳዊ ሐብቶቹ በአንፃራዊነት ካጎለበተው የምርምር አቅምሙ በመነሳት ዩንቨርስቲው የምርምር ፕሮጀክቶች መቅረጽን፣ ማጎልበትን እና ማካሄድን በተመለከተ በአጠቃላይ የማዕከሉ የሥራ አመራርና እንቅስቃሴ ላይ እንደከተማው አስተዳደር ሙሉ ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

**፲፱. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩. ካቢኔው ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪. ቦርዱ የዚህን አዋጅ ድንጋዎች ለማስፈፀም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች ወይም ልምዳዊ አሰራሮች በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ ለተደነገጉ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

**፳፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ አዋጅ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የሚፀና ይሆናል፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፴ ቀን ፪ሺ.ህ፪ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

2. By virtue of its long standing experience in teaching and research emanating from its relatively developed research capacity in terms of human and material resources pertaing to the formulation, development and conduct of research projects the university shall have full responsibility as that of the city government on the overall management and activity of the garden.

**19. Power to Issue Regulation abnd Directives.**

1. The cabinet may issue regulation to impelement this proclamation.
2. The Board may issue directives and guidelines for the implementations of the provisions of this proclamation.

**20. Inapplicable Laws**

Proclamation, regulations directives or customary practices which are inconsistent with this proclamation shall have no effect on matters provid in this proclamation regulations directives and guidelines to be issued to implement the same

**21. Effective date**

This proclamation shall come into force on the date of its publication in the Addis Negari Gazette.

**Done at Addis Ababa**

**This 9th day of November 2009**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**